

፩27-1፪

# ለሰለቸው እግዚአብሔር መልስ አለው

የምንሠራው ሥራ፣ የምንኖረው ተደጋጋሚ የሆነ ኑሮ ስልችት ብሎን፣ "ምነው እንደ እከሌ ዓይነት ኑሮ፣ እንደ እከሌ ዓይነት ሥራ በኖረኝ" ያልንባቸው ጊዜያቶች ይኖሩ ይሆን? ችግራችን፣ ያ ሥራውና ኑሮውን የተመኘነው ሰው በምን ዓይነት አቋም ላይ እንዳለ አለማወቃችን ነው። እኛ ከምንገምተውና ከምናስበው በላይ ሕይወት እጅ እጅ ያለው፣ ኑሮ የሰለቸው "የት ጠፍቼ ልብረር" የሚል ሰው ይሆን ይሆናል። የእኛን ሕይወት ተመልክቶ እርሱ ደግሞ እኛ የምንኖረውን ዓይነት ኑሮ ለመኖር በበኩሉ ይመኝ ይሆናል። በመጽሐፍ ቅዱስም ኑሮን በተለያየ አቅጣጫ ተምልክቶ ተለዋዋጭና አዲስ ነገር ያጣበት ሰው "ሁሉ ነገር አሰልቺ ነው፤ አሰልቺነቱንም ሰው በቃል ገልጦ ሊናገረው እንኳን አይችልም፤ ዓይን አይቶ አይጠግብም፣ ጆሮ ሰምቶ በቃኝ አይልም። ቀድሞ የሆነው ነገር እንደ ገና ይሆናል፤ አሁንም የሚያደገው ነገር ሁሉ ያው ቀድሞ የተደረገው ነው፤ ስለዚህ በመላው ዓለም አዲስ ተብሎ የሚሠራ ምንም ነገር የለም" አለ (መክብብ 1፥8-9)።

የዓለም ሰዎች በተለይ በሰለጠነው ዓለም ውስጥ የሚኖሩ ጥሩ ኑሮ ሊያስኖራቸው የሚችል በቂ ንብረት አጥጋቢ ሥራ ያላቸው የሚፈልጉትን በሚፈልጉት ጊዜና ሰዓት ማግኘት የሚችሉ ሕይወት ሰልችቶአቸውና እጅ እጅ ብሏቸው የራሳቸውን ሕይወት በገዛ እጃቸው የሚያጠፉ ሰዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁጥራቸው እያደገ በመሄድ ላይ ነው። ክርስቲያኖችስ ይህን የመሰለ የሕይወት መሰልቸት ይኖርባቸው ይሆን? ሰው በመሆናቸው ከዓለማውያን የተለየ ልዩ ስሜት ባይኖራቸውም፥ ይህን ስሜት የሚያጠፉበት ምድራዊ የሆነ ሳይሆን ሰማያዊ የሆነ መፍቻ ቁልፍ አላቸው።

የምንኖረው ዕለታዊ ኑሮ ሲደጋገምና ሁልጊዜ ተመሳሳይ ሲሆንብን፣ ስልችት ይለንና ለመኖር ያለን ፍላጎታችን የሞተና የቀዘዘቀ ይሆናል። ከዚያ ከሰለቸን ሕይወት ውስጥ አውጥቶ ልዩ ዓለም ውስጥ የሚያስገባን ልዩ ኃይል በኖረ ብለን ብዙ ጊዜ እነመኛለን። ይህን ዓይነቱ ሕይወት የሰለቻቸው ሰዎች ከእውነት ሸሽተው ለመኖር ሲሞክሩ ይታያሉ። አንዳንዶች ደግሞ በልዩ ልዩ መድኃኒት አዕምሮአቸውን በማደንዘዝ እራሳቸውን ደልለው ለመኖር ሲሞክሩ ይታያሉ። ብዙዎቻችን በኑሮአችን አዳዲስ ነገር የማየት ዕድል የለንም። ከቦታ ወደ ቦታ እንደልባችን መዘዋወር አንችልም። ዓይናችን ዘወትር ማየት የለመደው አንድ ዓይነት ነገር ነው። ይነጋል በዕለታዊ ሥራችን ተመሳሳይ የሆነ ነገር እየፈጸምን ጎንበስ ቀና በማለት ውለን ወደ ቤታችን እንገባለን። ነገ፣ ተነገወዲያም ከዚያ ወዲያ ሳምንቱን፣ ወሩን፣ ዓመቱን ሙሉ ሕይወታችን ተመሳስይና አንድ ዓይነት ነው። ችክ ሲልብን ይህን ከመሰለ ሕይወት አስፈንጥሮ የሚያወጣን ሁኔታ እንዲፈጠር እነመኛለን፤ ካጣንም እራሳችን ለመፍጠር እንሞክራለን።

## ሕይወትን እንዳለ እንቀበለው

ስለ ሕይወት ጥሩ አመለካከት ከሌለን በእርግጥ ኑሮ ችክ ሊልብን ይችላል። እርግጥ ነው የብዙዎቻችን የኑሮ ዓይነት ሁልጊዜ ተመሳሳይና ተደጋጋሚ ነው። የእቤት እመቤት የሆነችዋ ሴት ጥዋት ተነስታ ባሏ ተሰናብቷት ሥራው ከሄደበት ሰዓት ጀምሮ ቀኑን ሙሉ በቤቷ ውስጥ ጎንበስ ቀና ስትል ትውላለች። ትላንት ማታ ሳይታጠቡ ያደሩ ሳህኖች ተቆልለው ይጠብቋታል፤ የቤት ጽዳቱ፣ ልብስ አጠባው፣ ምግብ ቅቀላው፣

ሁሉም በየተራቸው ይጠብቋታል። ቀኑ፣ ሳምንቱ፣ ወሩ ዓመቱ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ያልፋል። ሰው ነችና ኑሮ ሳይሰለቻት አይቀርም። በዚህ ጊዜ ይህን ከመሰለ ተደጋጋሚ ሕይወት የምትወጣበትን መንገድ ትፈልጋለች። ኑሮ ችክ ስላለባት ብቻ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሳትጠይቅ በዚያ ስፍራ እንድታገለግል እግዚአብሔር አስቀምጧት እንደ ሆነ እራሷን ሳትጠይቅ በችኮላ ውሳኔ እንድትወስድ ትገደዳለች።

የእግዚአብሔር ፈቃድ አልጠይቀችምና ወዲያው አዲሱ የለወጠችው ሥራና የሕይወት አቋም ሳታውቀው ስልችቷት እራሷን ታገኘዋለች። መኖር በዚህ መልክ ሲሰለች ሰው የራሱን እርምጃ ከመውሰዱ በፊት እግዚአብሔር ለዚህ ችግር መውጫ መልስ ይኖረው ይሆን? ከዚህ በፊት ተደጋጋሚ ሥራ በመሥራት የሚሰለች ሕይወት ውስጥ ቢኖሩም፤ ይህንን የሚሰለች ሕይወት ተቋቁመው ይኖሩ ታሪካቸው በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈ ሰዎች ይኖሩ ይሆን?

ስልችት የሚል ዓይነት ኑሮ እንዲኖሩ፣ ፍጹም ችክ የሚል ዓይነት ሥራ እንዲሠሩ ከተጠሩት ሰዎች መካከል አንዱ ነብዩ ሕዝቅኤል ነው። ሕዝቅኤል ያን የመሰለ ስልችት የሚል ሕይወት ታግሶ ማለፍ የቻለው እግዚአብሔርን በፍጹም ልቡ "አድርግ" ያለውን ነገር ማድረግ እንዳለበት ተረድቶ እግዚአብ ሔርን በመታዘዙ ነው። እግዚአብሔርም በዚህ ምክንያት ሕዝቄል ያን የመሰለ የሚሰለች ሕይወት እንዲ ያልፍ ልዩ የሆነ ኃይል ሰጠው።

የእሥራኤል ሕዝብ እንደተለመደው በእግዚአብሔር ላይ በአመጸበትና ወደ ጣኦት አምልኮቱ በተመለሰ ጊዜ፥ የእሥራኤልን ሕዝብ ለመቅጣት የባቢሎኑን ናቡከደናጾርን እንደ ጠላት አድርጎ አስነሳባቸው። ናቡከደናጾር ወደ ኢየሩሳሌም 3 ጊዜ ለተለያየ ዓላማ ሄደ። ይኸውም፥

1ኛ. ወደ ፊት በምርኮ ወደ ባቢሎን የሚወሰዱትን የእሥራኤልን ሕዝብ ለማስተዳደር እንዲችሉ በቅድሚያ ለማሰለጠን ጥቂት ወጣቶችን መርጦ ወደ ባቢሎን ይዞ ሄደ። በዚህ ጊዜ ከተወሰዱት ወጣቶች መካከል፥ ዳንኤልና ጓደኞቹ ይገኙበታል።

2ኛ. ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶ ብዙ የእሥራኤላውያን ምርኮኞችን ወደ ባቢሎን ይዞ ሄደ። በዚህን ጊዜ ነው ነብዩ ሕዝቄል የተወሰደው።

3ኛ. ነቡከደናጾር ለሶስተኛ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶ ከተማዋንና ቅጥሯን አፈራረሰ።

ሕዝቄል ወደ ባቢሎን ከተወሰደ በኋላ እግዚአብሔር በማያጠራጥርና ግልጽ በሆነ ሁኔታ ወደ ልዩ አገልግሎት ጠራው። *"የሰው ልጅ ሆይ! እነሆ ወደ እስራኤል ሕዝብ እልክሃለሁ፤ እነርሱ ዐምጸው በጠላትነት በእኔ ላይ ተነሥተዋል፤ የቀድሞ አባቶቻቸው እንደ ነበሩት ሁሉ አመጻቸውን አልተውም። እነርሱ እልኸኞች ናቸው፤ እኔንም ማክበር ትተዋል፤ ስለዚህ እኔ እግዚአብሔር የምነግራቸውን ሁሉ እንድታስታውቃቸው ወደ እነርሱ እልክሃለሁ። እነዚያ አመጸኞች ቢሰሙህም ባይሰሙህም ነብይ በመካከ ላቸው መኖሩን ያውቃሉ"* (ሕዝ. 2፥3-5)።

ሕዝቄል እግዚአብሔር የሚልከው በጣም አስቸጋሪ በሆኑ ሕዝቦች መካከል እንደ ሆነ ቀደም ብሎ ተረድቷል። ሕዝቄል የተመለከተው የመልዕክቱን ከባድነትና የሕዝቡን አስቸጋሪነት ሳይሆን እግዚአብሔር እንደ ላከውና መልዕክቱን ለሕዝቡ በማስተላለፍ የጠራውን አምላክ መታዘዙን ነው። እግዚአብሔር ሕዝቄልን እንዲያደርግ የጠየቀው ነገር አስቸጋሪና በጣም የሚሰለች ነበር። ይሁን እንጂ ሕዝቄል የታዘዘውን በትዕግሥት መፈጸም ቻለ።

በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሕዝቄልን እንዲያደርግ የጠየቀው *"ወደ ቤትህ ሂድ፤ በርህንም ዘግተህ ተቀመጥ"* (ሕዝ. 3፥24) የሚል ነበር። ምን ዓይነት ትዕዛዝ ነበር? እርግጠኞች ነን ሕዝቄል እግዚአብሔር ይህን የመሰለ ትዕዛዝ ይሰጠኛል ብሎ እንዳልገመተ። ምናልባት፥ እግዚአብሔር ሲጠራው፥ እንደ ነብዩ ኢሳያስ በንጉሥ አደባባይ፥ ከንጉሥ ጋር ገባታ አብሮ እየቀረበ በዓለም ሁሉ ታዋቂና ዝነኛ ሆኖ በክብር የሚያገለግል መስሎት ይሆናል። ወይንም እንደ ዳንኤል በባቢሎን ግዛት ውስጥ ስልጣን ኖሮት ማስተዳደር

የሚችል ሳይመስለው አይቀረም። ምናልባትም የባቢሎን ጠቅላይ ሚኒስትር እሆናለሁ ብሎ ሳይገምትም አልቀረም። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ሕዝቄልን ያዘዘው ከባድ ሥራና ኃላፊነት የሚጠይቅ አልነበረም። ያለው "ወደ ቤትህ ገብተህ በርህን ዘግተህ ተቀመጥ" ብቻ ነበር።

ሕዝቄል እንዲያደርግ የተጠየቀው ነገር በሰው አስተሳሰብ ሞኝነት ቢመስልም፥ በሩን ዘግቶ ተቀመጠ። ከውጪው ዓለም ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል" የሚለው መልዕክት አልነበረውም። ምንም እንዳይናገር እግዚአብሔር ከልክሎት ነበር። *"ይህን ዐመጸኛ ሕዝብ ማስጠንቀቅ እንዳትችል እንደበትህ እንዲተሳሰር አደርገዋለሁ"* (ሕዝ. 3፥26) ብሎት ነበር። ከውጪም ሆነ ከውስጥ የምሰማው ምንም ዓይነት ድምጽ አልነበረም። በሕይወቱ ፍጹም ጸጥታ የሆነበት ጊዜ ነበር። ነጋም፣ መሸም የሚመለከተው አዲስ ነገር አልነበረም። ያው የለመደው የቤቱን ጣራና ግድግዳ ነበር። ዝም ብሎ ቤቱን ዘግቶ መቀመጥ ሕዝቄልን ምን ያህል ሰልችቶትና ችክ ብሎበት ይሆን? ይሁን እንጂ ሕዝቄል እግዚአብሔር "ይበቃሃል፤ ና ውጣ!" እስከሚለው ድረስ በትዕግሥት ቤቱን ዘግቶ ተቀመጠ። እግዚአ ብሔር እንድንሠራው የሰጠን የሥራ ኃላፊነት ችክ ብሎብን ይሆን? እስቲ የእኛን ሥራ ከሕዝቄል ጋር እናስተየየው። እርግጠኛ ነኝ የሕዝቄልን ያህል የሚሰለች እንዳልሆነ።

ከተወሰነው ጊዜ በኋላ ሕዝቄል የዘጋውን በር ከፍቶ እንዲወጣ ፈቀደለት። ይን ከመሰለ የሰለቸ ሕይወት ሲያውጣው ሕዝቄል ምን ይህል ደስ ብሎትና ፈንድቆ ይሆን? ይሁን እንጂ ይሄ የሚሰለች ወይንም ችክ የሚለው ሕይወት ሳያንሰው፥ ከዚያ የከፋና የሚሰለች ሕይወት ውስጥ አስገባው። እግዚአብሔር ለሕዝቡ ሊያስተላልፍ የሚፈልገውን መልዕክት በልዩ መንገድ ሕዝቄል እንዲያቀርብ ሌላ የሚሰለች ሥራ እንዲሠራ ትዕዛዝ ሰጠው። *"እንግዲህ በግራ ጎንህ ተኛ፤ እኔም የእሥራኤልን ኃጢአት ሁሉ በአንተ ላይ እጭናለሁ፤ ስለ እነርሱም በደል እየተሰቃየህ 390 ቀኖች በዚያ ትቆያለህ፤ እነርሱን በምቀጣበት በእያንዳንዱ ዓመት ልክ አንድ ቀን እንድትቀጣ ወስኛለሁ፤ ያንንም ከፈጸምህ በኋላ ተዛውረህ በቀኝ ጎንህ በመተኛት እንደገና ስለ ይሁዳ በደል አርባ ቀን ትሰቃያለህ፤ ይህም እነርሱን በምቀጣበት በእያንዳንዱ ዓመት ልክ ይሆናል ማለት ነው"* (ሕዝ. 4፥4-6)።

ሕዝቅኤል እግዚአብሔር እንዳዘዘው ሰውነቱን በገመድ አስሮ በቀኝ ጎኑ ተኛ። ሰዎች እንደ ሞኝ እየተመለከቱት በአጠገቡ ያልፋሉ። ምንም ዓይነት ንግግር እንዲያደርግ አልተፈቀደለትም ነበር። የእርሱ ሥራ ሳይገላበጥ በቀኝ ጎኑ መተኛት ነበረበት። በቀኝ ጎኑ 390 ቀኖች ምንም ሳይገላበጥ ምንም ዓይነት በቃላት የሚገለጽ መልዕክት ሳያስተላልፍ ጸጥ ብሎ ተኛ። እግዚአብሔር የወሰነው 390 ቀናት ሲያልፍ ቀጥሎ ደግሞ በግራ ጎኑ ለ40 ቀናት እንዲተኛ ትዕዛዝ ተሰጠው። ሕዝቄልም "አሁንስ በዛ! ሰለቸኝ" ሳይል ጸጥ ብሎ እግዚአብሔር እንደ ነገረው አደረገ። በጠቅላላው ለ430 ቀናት አንድ ቦታ ሳይታመሙ ተኝቶ መከረም ምን ያህል የሚሰለችና የሚቸክ ሕይወት እንደ ነበር መረዳት አያስቸግርም። እነዚያ 430 ቀናት ትርጉም ነበራቸው። ብዙዎች የተለያየ ትርጉም ይሰጡታል። አንደኛው፥ እሥራኤል በእግዚአብሔር ላይ በአመጸች ጊዜ በባርነት ለ430 ዓመት ግብጽ የቆየችበት ጊዜ ነው ይላሉ። አንዳንዶች ደግሞ እሥራኤል በተለያዩ የንጉሦች አገዛዝ ሥር በነበረችበት ጊዜ ከእግዚአብሔር የኮበለለችበት ጊዜ ነው ይላሉ። ያም ሆነ ይህ፥ ይሄ 430 ቀኖች የሚያመለክተው እግዚአብሔር በእሥራኤል የሚያደርገውን የቅጣት ዘመን የሚገልጽ ነበር። ጥያቄያችን እዚህ ላይ፥ ሕዝቄል 430 ቀን እንደታሠረ በአንድ ጎኑ መተኛት የቻለበት ምክንያት ምን ነበር?

**በሚቀጥለው ክፍል እንክንገናኝ፥ የጌታ ጸጋና ሰላም ከሁላችን ጋር ይሁን።**